Seattle Office of Labor Standards

# Grocery Employee Hazard Pay Ordinance **የተጨባጭ እውነታ ሰነድ**

Grocery Employee Hazard Pay Ordinance (የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር ሠራተኛ የክፍያ ማዘዣ) የተወሰኑ በሲያትል ውስጥ ያሉ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮች በ COVID-19 ድንገተኛ አደጋ ወቅት በችርቻሮ መደብራቸው ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞች በሰዓት $4 የአደጋ አበል እንዲከፍሉ ያስገድዳል። ይህ የአደጋ አበል **ፌብሩዋሪ 3፣ 2021** ከ 12:01 AM ጀምሮ እስከ COVID-19 የሲቪል ድንገተኛ ጊዜ ማብቂያ ድረስ በሥራ ላይ ይቆያል።

## የትኞቹ ኩባንያዎች በዚህ ሕግ ተገዢ መሆን አለባቸው?

ይህ ሕግ በሸቀጣ ሸቀጥ መደብር የንግድ ሥራ ላይ በተሠማሩ፣ ከሚከተሉት አንዱን የሆኑ የችርቻሮ መደብሮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡-

1. መጠናቸው ከ10,000 ካሬ ጫማ በላይ የሆነ እና በዋንኛነት በችርቻሮ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር ሥራዎች ላይ የተሠማሩ፤ ወይም
2. መጠናቸው ከ85,000 ካሬ ጫማ በላይ ሆኖ፣ ከዚህ ውስጥ 30 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የሽያጭ መፈጸሚያ ቦታቸው ለሸቀጣ ሸቀጥ ሽያጭ የተመደበላቸው።

"የሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮች" የሚከተሉትን የሚያካትቱ ቢሆንም በእነዚህ ብቻ ግን የተወሰኑ አይደሉም፡- ትኩስ ምርት፣ ሥጋ፣ ዶሮና እንቁላል፣ ዓሣ፣ የዴሊ ምርቶች፣ የወተት ተዋፅኦዎች፣ የታሸጉ እና በረዶ የሠሩ ምግቦች፣ የተጋገሩ ምግቦች፣ እና/ወይም የተዘጋጁ ምግቦች።

በዚህ ሕግሽፋን ለማግኘት፣ የንግድ ሥራው በዓለም ዙሪያ ከ500 በላይ ሠራተኞችን መቅጠር ይኖርበታል። ሕጉ ሃያ አራት ሰዓት የሚሠሩ ሁሉን አቀፍ ሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮች ወይም በዋንኛነት የተወሰኑ ዓይነት ሸቀጦችን በሚሸጡ የምግብ ሱፐርማርኬቶች ላይ **ተፅዕኖ አይኖረውም**።

## የትኞቹ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር ሠራተኞች የአደጋ አበል ሊከፈላቸው ይገባል?

ይህ ሕግ ሽፋን በተሰጣቸው በሲያትል ውስጥ በሚገኝ የሸቀጣ ሸቀጥ መሸጫ ቦታ ላይ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር የንግድ ሥራዎች ለሚሠሩ ተቀጣሪ ሠራተኞች ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## ምን ያክል የአደጋ አበል መከፈል አለበት?

ሠራተኞች የአደጋ አበል **$4 በሰዓት** ሊከፈላቸው ይገባል። ከካሣ ክፍያ፣ አበሎች፣ ኮሚሽን ክፍያዎች እና ጉርሻዎች በተጨማሪ የአደጋ አበል ለሸቀጣ ሸቀጥ መደብር ሠራተኛ ለአቀረበው አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ነው።

የግሮሰሪ የንግድ ሥራዎችበዚህ የክፍያ ትዕዛዝ ምክንያት ሌሎች ለሠራተኛ የሚከፈሉ ካሣ ክፍያዎችን ለመቀነስ ማናቸውንም እርምጃ እንዳይወስዱ ይከለከላሉ።

## የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር ንግድ ሥራዎች እንዲህ ማድረግ አለባቸው፡-

- ሠራተኞች ለሠሩበት ሰዓት በመደበኛነት ከሚከፈለው ክፍያ በሚከፈልበት ተመሳሳይ የክፍያ ጊዜ ላይ የአደጋ አበልን መክፈል፤
- ከሌሎች ክፍያዎች ተነጥሎ በክፍያ ደረሰኝ ላይ የአደጋ አበልን እንዲጠቀስ ማድረግ፤
- ለሠራተኞቻቸው ወቅቱን የጠበቀ Notice of Employment Information (የሥራ ቅጥር መረጃ ማስታወቂያ)፣ በ Wage Theft Ordinance (የደመዎዝ ክፍያ ስርቆት ክፍያ ማዘዣ)መሠረት መስጠት፤ እና
- ከማርች 5፣ 2021 በፊት ከበቀል እርምጃ ነጻ መሆን መብትን ጨምሮ በዚህ ሕግ የተሰጡ መብቶችን በተመለከተ ለሠራተኞች የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠት። ማስታወቂያው በእንግሊዘኛ እና በመደብር ውስጥ በሚሠሩት ሠራተኞች ዋንኛ ቋንቋ የተጻፈ መሆን አለበት።

## SEATTLE OFFICE OF LABOR STANDARDS

የእኛ ተልዕኮ ጥልቅ አስተሳሰብ ባለው የማኅበረሰብና የንግድ ሥራ ተሳትፎ፣ ስትራቴጂክ ትግበራና የፈጠራ ሥራ የፖሊሲ ዝግጅት አማካይነት የሠራተኞችን ደረጃ ማሳደግ ሲሆን፣ ለዘርና ለማኅበራዊ ፍትሕ መከበርም ቁርጠኛ አቋም አለን።

**አገልግሎቶቻችን**

ቅሬታዎችን መመርመር

ለሠራተኞች ባሉበት መድረስ

ለንግድ ሥራ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት

ግብዓቶችና የማስተላለፍ ሥራዎች

የቋንቋ ማስተርጎምና የጽሑፍ ትርጉም አገልግሎት ማግኘት ይቻላል። የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ተገቢነት ያለው መስተንግዶ ይሰጣል። አገልግሎቶች ነጻ ናቸው።

**ተጨማሪ መረጃ**

ወደዚህ ይደውሉ፡- (206) 256-5297

ኢሜይል፡- laborstandards@seattle.gov

ይህን ይጎብኙ፡-
seattle.gov/laborstandards



*በዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረበው መረጃ ሕጋዊ ምክር ባለመሆኑ ሕጎችና ደንቦችን በመተካት አገልግሎት መስጠት የለበትም። ስለዚህ ሕግ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የእኛን Grocery Employees Hazard Pay Ordinance የድር ገጽ ይጎብኙ።*